የሰ/መ/ቁ. 44025

ሐምሌ 22 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች**፡- 1. ወ/ሪት ፀሃይ ሃይሌ - ቀረበች

2. ወ/ሪት ጤናዬ ሃይሌ - ቀረበች

3. ወ/ሪት ኤልሳቤጥ ሃይሌ - አልቀረበችም

4. መስፍን ሃይሌ - አልቀረቡም፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ፈልቃ ቤኛ - ጠበቃ ሙላት ፈለቀ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 65587 ጥር 15 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ክርክሩ በአሁኖቹ አመልካቾች ከሣሽነት የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካቾች ተጠሪን የከሰሱት ከአባታችን ልናገኝ የሚገባውን የውርስ ድርሻ ይዛ እየተጠቀመች ስለሆነ ውርስ አጣሪ ተሾሞ ድርሻችን እንዲለይ ይታዘዝልን በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ለክሱ በሰጠችው ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበች ሲሆን፣ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን በመቀበል ክሱን ውድቅ አድርጐአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቾች ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረባቸው ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካቾች የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚሉበትን ምክንያት በመግለጽ አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአመልካቾች የቀረበው የውርስ ይጣራልን ክስ /ጥያቄ/ በይርጋ ቀሪ ነው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ የአመልካቾች አባት ሚስት ናት፡፡ የአመልካቾች አባት እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ አመልካቾች በዚሁ የአባታቸው እና የተጠሪ የጋራ ነው የተባለው ቤት ውስጥ በአባታቸው እና በተጠሪ ሲያድጉ ቆይተዋል፡፡ አባታቸው ከሞቱም በኂላም ተጠሪ እንደእናት በመሆን ስታሳድጋቸው እንደቆየች እና ንብረቱንም በጋራ ይዘው ሲያስተዳድሩት እንደነበር አመልካቾች በክርክራቸው ገልጸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት እንዲለይ እና የአባታቸውን ድርሻ በወራሽነታቸው ማግኘት ይችሉ ዘንድ ክስ የመሰረቱት ተጠሪ እነሱ ባላወቁት ምክንያት ከቤት ወጥታ በመሄድ ዘመዶቼናቸው ከምትላቸው ሰዎች ጋር በመቀመጥዋ እንደሆነ በሰበር አቤቱታቸው ላይ በግልጽ በማመልከት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪም ለሰበር አቤቱታው በጽሑፍ መልስ የሰጠች ሲሆን በአመልካቾች ክርክር በግልጽ በተነሱት ነጥቦች ላይ ምንም ማለት አልቻለችም፡፡ በዚህ ረገድ የመረጠችው በዝምታ ማለፍ ነው፡፡ በእርግጥ ከዚህ በፊት በሰበር ችሎቱ የተሰጡትን ውሳኔዎች በመጥቀስ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ትክክል ነው እንዲባልላት ተከራክራለች፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ችሎቱ ከጠበቃው ላቀረበው ጥያቄ ከተሰጠው ምላሽ ተጠሪዎች በፍሬ ነገር ረገድ ያነሱት ክርክር ትክክል እንደሆነ ለማረጋጥ ችለናል፡፡ የተጠሪ ጠበቃ ለቀረበለት ጥያቄ በሰጠው መልስ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ንብረቱ/ቤቱ/ በአመልካቾች ይዞታ ሥር እንደሆነ አረጋግጦአል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካቾች የውርስ ድርሻ የጠየቁበት ንብረት ሁለቱም ወገኖች ይዘውት በጋራ ሲያስተዳድሩት የነበረ በመጨረሻም (ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ) በአመልካቾች ይዞታ ሥር ያለ ነው፡፡ አመልካቾች ወደ ክስ ያመሩትም ንብረቱ በዚህ ደረጃ ላይ እንዳለ ተጣርቶ የአባታቸው ድርሻ እንዲታወቅና ወራሽነታቸው ለእነሱ እንዲሆን እንዲወሰንላቸው እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ እውነታው ይህ ከሆነ ደግሞ ንብረቱ በተጠሪ እጅ (ተይዞ) እንደቆየ በማድረግ የተጠሪን የይርጋ መቃወሚያ ተቀባይነት ይኖረዋል የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪ የሰበር ችሎቱ በሰበር መ/ቁ. 24675 እና 28317 የሰጣቸውን ውሳኔዎች በመጥቀስ ያቀረበችው ክርክርም እንዳየነው ውሳኔዎቹ የተሰጡት በዚህ መዝገብ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር የተለየ በሆነ ፍሬ ነገር ላይ በመመስረት በመሆኑ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካቾች ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል፡፡ በማለት የወሰኑት በፍትሐብሔር ሕጉ የተቀመጠውን የይርጋ ድንጋጌ እና የይርጋ መሰረተ ሃሳብ እንዲሁም የክርክሩን ፍሬ ነገር እግንዛቤ ውስጥ ባለማስገባት በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ